# የወያኔ ግፍና የሕዝባችን ሮሮ ቀጥሏል

## ከኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ
## የተሰጠ መግለጫ

**ሐምሌ 10 ቀን 2003 ዓ.ም.** ( July 17, 2011 )

*በኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር አካባቢ በመተማ፣ በቋራና በሌሎች ቦታዎች የሚገኙ ወገኖቻችን ተወልደው ካደጉበት ቀያቸው በቅርቡ በወያኔ ወታደራዊ ኃይል በግድ እየተፈናቀሉ ወደ ሌላ ሥፍራ እንዲሠፍሩ እየተገደዱ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም በነዚሁ ቦታዎች መጠነ ሰፊ የሆነ በወያኔ ጦር በመሥፈር ላይ እንደሚገኝ አንዳንድ ተጨባጭ መረጃዎች ያመለክታሉ።*

*በአካባቢው የሚገኙት የአምባገነኑ የወያኔ ባለሥልጣናት ለዚህ እኩይ ተግባራቸው ለሕዝቡ የሚሰጡት ማሳሳቻ ምክንያት ታላቁን የአባይ ግድብ ለመገንባት በምናደርገው ጥረት የግብፅና የሱዳን አቋም አስተማማኝ ስላልሆነ የአካባቢውን ፀጥታና ደህንነት ለማስጠበቅ ነው የሚል ነው። "ስምሽ ማነው ቢሏት ቤቴ አራት ኪሎ ነው" እንዳለችው ኮረዳ እነአቶ መለስ የሚናገሩትና የሚሠሩት ሁሉ እድሜ ልካቸውን ሳይጣጣሙ እነሆ 20 ዓመት አለፋቸው።*

*ከዛሬ ሶስት ዓመት በፊት በጐንደር ክፍለ ሀገር በቋራ ወረዳ ውስጥ በነፍስ ገበያና በሌሎችም ሥፍራዎች በሰፋፊ እርሻ ላይ ተሰማርተው የነበሩ በኢትዮጵያውያን ንብረታቸው እንደተቃጠለ፣ እንደተወረሰና ሠራተኞቻቸው በወራሪው ሱዳን ጦር ወታደሮች ተገደው ወደ ሱዳን ተወስደው ለእሥር ተዳርገው እንደነበር በሰፊው መዘገቡ አይዘነጋም።*

*በዛን ወቅት ይህ የድንበር ኰሚቴ የወገኖቻችንን ጩኸት ለዓለም ኅብረተሰብ ይፋ ማድረጉና የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮም እነዚህ ወገኖቻችን ከታሠሩበት ከዚያው ከሱዳን ወህኒ ቤት ያሰሙትን የ"ድረሱልን" የሰቆቃ ጥሪ ማሰራጨቱ እየታወቀ አቶ መለስ ካላንዳች እፍረት ለኢትዮጵያ ሕዝብ "እደግመዋለሁ" እያሉ "አንድም ኢትዮጵያዊ የተፈናቀለ የለም" ሲሉ የተናገሩትን ዓይን ያወጣ ቅጥፈት የኢትዮጵያ ሕዝብ ምን ጊዜም ቢሆን የሚረሳው አይደለም። አልፈው ተርፈውም የሱዳን መንግሥት የኢትዮጵያ ወራሪነት ለዓመታት ተሸክሞ የኖረ እርቀ አስተዋይ መንግሥት ነው ሲሉ የሰጡት የሐሰት የምስክርነት ቃል እኝህ ሰው የሱዳን መንግሥት ነገረ-ፈጅ ናቸው ወይስ እውን እሳቸው እንደሚሉት የኢትዮጵያ ሕዝብ መሪ ናቸውን? እስከማለት የተደረሰበትን ሁኔታ እያንዳንዱ የኅብረተሰብ ክፍል በፀፀት የሚያስታውሰው ነው። ለነገሩማ አቶ መለስ ከዛሬ ሶስት ዓመት በፊት በሚሊኒየም ምሽት ዝግጅት ጊዜ የተለያዩ የሀገራዊ ባሕል ዘፈኖች ሲቀርቡ ቁጭ ብለው በጽሞና ሲመለከቱ የነበሩት " የእኛ መሪ" የሱዳን ዘፈን ሲሰሙ ከተቀመጡበተ ወንበር ሥር የኤክትሪክ ምገድ የነዘራቸው ይመስል ከመቅጽበት ተስፈንጥረው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያሳዩት ዳንኪራ የአቶ መለስ የወገናዊነት ሚዛን የት ላይ እንደደፋ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተረድቶ ስለ እርሳቸው ምንነት እርሙን ያወጣበት ቀን ነበር።*

*አገራችን ኢትዮጵያ እግዚአብሔር ጥሎ ስለአልጣላትና በሶማሊያ የረባ ማእከላዊ መንግሥት ባለመኖሩ ካልሆነ በቀር በአቶ መለስ እምነት ኦጋዴን እስከ ዛሬ በኢትዮጵያዊነቱ ባልሰነበተ ነበር። እርሳቸው የሚያስረክቡት ሰው በማጣታቸውና በሶማሊያ በኩል ፈርሞ የሚረከብ ሰው ባለመገኘቱ እንጅ እስካሁን በምሥራቅ ያለው ወሰናችን አዋሽ ወንዝ ዳርቻ በሆነ ነበር።*

*ታዲያ በ17 ዓመት የጫካ ዘመን ለተደረገለት እርዳታ ሁሉ ወሮታውን ለመክፈል እላይ እታች የሚለው የአቶ መለስ ጨቋኝ አገዛዝ እላይ በጠቀስናቸው ሥፍራዎች በቅርቡ ያሰማራቸው የወያኔ ሠራዊት "የአካባቢውን ደኅንነት" ለማስጠበቅ ነው በሚል ሽፋን ወገኖቻችን ከቀያቸው ቢያፈናቅሉና የቁም ስቅላቸውን ቢያሳዩአቸው ፈጣሪ ምሕረቱን እንዲያመጣ፣ ሕዝቡን እንዲያጠናክርልን ከመማፀን ባሻገር የጋራ አንድነታችንን አጠናክረን ይህን አገርን የማፍረስ ሥራ ልናወግዘውና ልንታገለው ይገባል።*

*ወገኖቻችን ከሚፈናቀሉበት የድንበር ቦታዎችና ከተሞች አንዱ ታሪካዊው የመተማ ከተማ ነው። ይህ ሥፍራ እንደነ አፄ ቴዎድሮስ የመሳሰሉ ቀደምት ጀግና መሪዎቻችን የተወለዱበትና አድገው ሀገርን አንድ ለማድረግ የተንቀሳቀሱበት፣ እንዲሁም አፄ ዮሐንስ ለአገራቸው ነፃነት ሲሉ ከድርቡሾች ጋር ሲፋለሙ አንገታቸው በሰይፍ የተቀላበት ታሪካዊ ቦታ ነው። ከጥቂት ወራት በፊት የከተማው ሕዝብ የዮሐንስን ቤተ ክርስቲያን ለማሳደስ ፈልጎ ማሳደስ እንደማይችል በካባቢው የወያኔ ሹሞች ተነግሮታል። ድሮስ ታሪክን ለማጥፋት ምሎ ተገዝቶ ከተነሣ አካል ከዚህ የተለየ ምን መልስ ይጠበቃል!! ሲሆን ሲሆን ይህን የመሰለ ታሪካዊ ሥፍራ መንግሥት ነኝ ባዩ ካለምንም የሕዝብ ማሳሰቢያ በራሱ ወጪ ቤተ ክርስቲያኑን አድሶ የአገርን ታሪክ ለትውልድ እንዲተላለፍ ማድረግ በተገባው ነበር። ይህ ሳይሆን ደግሞ፤ ሕዝቡ ቤተ አምልኰቱን በራሱ ወጪ ለማሳደስ ሲነሣ ሌላው ቢቀር እንዴት እንቅፋት ይፈጥርበታል? ጉዳዩ ከኋላ ያለው ሀገርን አሳልፎ የመስጠት ሥውር ደባ ተግባራዊ ለማድረግ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ሥራ መሆኑ ነው።*

*የአርማጭሆ ወረዳ ሕዝብም ተመሳሳይ የከፋ ችግር እየገጠመው ነው። ኅብረተሰቡ በእርሻ ወቅት ከደጋው ወደ ቆላው የድንበር አካባቢ እየወረደ ለዘመናት ያርስበት የነበረውን ቦታ እንዳያርስ ተከልክሏል። ሕዝቡም የባእዳን ከበርቴዎች ከሕንድ፣ ከቻይና እና ከተለያዩ የዓረብ አገሮች እየመጡ ለም መሬት እየተሰጣቸው እንዲያርሱ ሲደረግ እንዴት እኛ ኢትዮጵያውያን ተወልደን ባደግንበት ሥፍራ ለማረስ ያውም ከእጅ ወደ አፍ ለሆነ ኑሮ እንከለከላለን በማለት በቁጭትና በንዴት አንጀቱ እያረረ ተቃውሞውን በማሰማት ላይ ይገኛል። ሕዝቡ ተቃውሞውን ለመግለፅ አስቦ ባለፈው ሰሞን ከሑመራ እስከ ጐንደር ያለውን አውራ መንገድ ለመዝጋት በዝግጅት ላይ እያለ በክልሉ የሚገኙት የወያኔ ሹሞችና ሠራዊቱ አባላት አስቀድመው በማወቃቸው እቅዱ ሳይሳካ መቅረቱን ካገኘነው መረጃ ለመረዳት ችለናል።*

*ሕዝቡ ዳር ድንበሩን፣ መብቱንና ንብረቱን ለማስከበር በሚያደርገው ትግል ውስጥ ሠራዊቱ ከጎኑ በመቆም ሕዝባዊ ወገናዊነቱን በተግባር ማስመስከር እንጂ እንቅፋት መሆን ፍጹም አይጠበቅበትም።*

*ሠራዊቱ ታማኝነቱ ለወያኔ ሕገ መንግሥት መከበር ነው እየተባለ ነጋ ጠባ ቢሰበክም፣ ታሪካዊ ኃላፊነቱና ብሔራዊ ግዴታው ግን የኢትዮጵያን ሕዝብ በዘርና በቋንቋ ሳይለይ የሁሉንም ደኅንነት በእኩል ዓይን መጠበቅና የሀገር ድንበር ማስከበር እንደሆነ ለአፍታም ሊዘነጋው አይገባም። ይሁን እንጅ፤ በተጻራሪው አገርን በማፍረስ እና ዳር-ድንበርን አሳልፎ በመስጠት በሚደረገው ተግባር ተሳታፊ ከሆነ፤ በአገር ክህደት ወንጀል በሕዝብና በታሪክ ፊት ተጠያቂ እንደሚያደርገው በጥብቅ ለማስገንዘብ እንወዳለን።*

*ባለፈው ወር አቶ መለስ በሰሜንና በደቡብ ሱዳን የሚታየውን የፀጥታ ችግር ለማስወገድ ሠራዊቴን እልካለሁ ብለው ሲያውጁ ለሰማው ሰው ሁሉ ነገሩ እንቆቅልሽ እንደሆነበት ግልፅ ነው። ምክንያቱም በእርሳቸው አዛዥነት በኦጋዴን፣ በጋምቤላና በሌሎችም የአገራችን ክፍሎች በሚኖሩ ሰላማዊ ሰዎች ላይ በተደጋጋሚ በተወሰደው የጅምላ ግድያ የተነሣ በዓለም ፍርድ ቤት ክስ ተመስርቶባቸው ወንጀላቸው በመጣራት ላይ የሚገኙት አቶ መለስ አሁን የሌላ አገርን ሕዝብ ፀጥታ ለማስከበር ጦሬን እልካለሁ ብለው ሲነሱ "የራሷ ሲያርባት የሰው ታማስላለች" የሚለውን የአበው አባባል እንድናስታውስ ያደርገናል።*

በባእድ አገር በሰላም አስጠባቂነት የሚሰማራ አንድ ሠራዊት በቅድሚያ የራሱን ወገን ደኅንነት የማስጠበቅ ኃላፊነትና ግዴታ እንዳለበት የሚታወቅ ነው።

የወያኔ ገዥ ቡድን በአገርና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እስከ ዛሬ የፈጸመውን ግፍንና ሴራ ሠራዊቱ ተገንዝቦ፤ በቀጣይ እርምጃው አፈሙዙን በኅብረተሰቡ ላይ ማነጣጠሩን አ ቁ ሞ ሕዝባዊነቱን ለመግለፅ አዲስ አቋም ይዞ እንዲነሣ በዚህ አጋጣሚ ጥሪ እናቀርባለን።

በክልሉ የምትገኝ ወገናችንም በየመንደርህና በየአጥቢያህ እየተሰበሰብክ መብትህን፣ ንብረትህንና የሀገርህን ድንበር ለማስከበር እስከ ዛሬ የምታካሂደውን ትግል በማጠናከር በጽናት ለመቀጠል ቆርጠህ መነሣት ይኖርብሃል። በአቶ መለስ የ20 ዓመታት አገዛዝ እስከዛሬ ያላየኸውን በጎ ምግባር ወደፊትም መቸውንም አታየውም። ምርጫው በጋራና በአንድነት ቆመህ ይህን አገር ከሀዲና ፀረ-ኢትዮጵያ ቡድን ለማስወገድ መታገል ነው።

እኛም በውጭ የምንገኝ የኅብረተሰቡ አካል ነን፣ የወገናችን ስቃይ ይሰማናል የምንል ሁሉ ቢያንስ ቢያንስ ለመብቱና ለሀገር ድንበር መከበር በመቆሙ ቁም ስቅሉን የሚያየውን የወገናችንን ችግር በመገንዘብ የሰቆቃ ድምፁን ልናስተጋባለት፤ መከራና ስቃዩ አይዞህ፣ አለንልህ በማለት ልንጋራው ይገባል። ትግሉ በይዘቱም በቅርጹም ሕዝባዊ ነውና ከድል መለስ የሚገታው አንዳችም ኃይል እንደሌለ ያለጥርጥር መናገር ይቻላል።

**የኢትዮጵያ የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት በቆራጥ ልጆቿ ይከበራል!**

**ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!**

**የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ**
**E-mail: ethiopianborders@gmail.com**